# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ከውጤታማ የሥራ ክንውኖች ጀርባ ያለው ጤናማ የፋይናንስ ሥርዓት

በአንድ ተቋም ውስጥ ጤናማ የፋይናንስ ሥርዓት መዘርጋቱ ውጤታማ አፈጻጸም እንዲኖር እገዛ ያደርጋል። በተለይም ከፍተኛ በጀት በሚንቀሳቀስባቸው ተቋማት ውስጥ ጤናማ የፋይናንስ ሥርዓት ሲኖር እያንዳንዱን በጀት በአግባቡ የማስተዳደርና የመምራት፤ ግዢንና ሽያጭን /ወጪንና ገቢን/ በተቀላጠፈና ግልጽ በሆነ መንገድ የማከናወን አቅም ይፈጠራል፤ ተቋሙ የሚያንቀሳቀሰው ካፒታል የቱንም ያህል ግዝፈት ይኑረው ጤናማ የፋይናንስ ሥርዓት እስከተዘረጋ ድረስ በኦዲት ምርመራ ወቅት የሚያጋጥሙ እንከኖች ይቀንሳሉ።

ውድ አንባብያን! በዛሬው ዕትማችን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የፋይናንስ ዘርፍ ተቋሙ ከሚያንቀሳቅሰው ከፍተኛ ኢኮኖሚ እና ከውጤታማ ሥራዎቹ ጀርባ እየተወጣ ያለውን ሚና ልናስቃኛችሁ ወድደናል። መልካም ንባብ!

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ከፍተኛ በጀት ከሚመደብላቸው የመንግሥት ተቋማት ውስጥ አንዱ ነው። ተቋሙ ከሀገር ውስጥ በጀትና ከውጭ ብድር እንዲሁም ከራሱ ገቢ በሚያገኘው ገንዘብ የኃይል ማመንጫ እና ማከፋፈያ ጣቢያዎች ግንባታ፣ የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮች ዝርጋታና እድሳት ያከናውናል። የግብዓት ግዢዎችና የኃይል ሽያጭም ያከናውናል። ተቋሙ ከስምንት ሺ በላይ ቋሚና ጊዜያዊ ሠራተኞችንም ያስተዳድራል። ከፍተኛ ፋይናንስ የሚያንቀሳቅሰው ይህ ተቋም ጤናማ የፋይናንስ ሥርዓት በመዘርጋት ከኦዲት ትችት የጸዳ ውጤት ማግኘቱ የዘርፉን አመራሮችና ሠራተኞች ትጋትና ጥንካሬ የሚያሳይና ለሌሎች ተቋማትም ምሳሌ የሚሆን ተሞክሮ ያለው ሆኖ አግኝተነዋል።



አቶ ደመረ አሰፋ

የተቋሙ የፋይናንስ ሥርዓት እንዴት እየተመራ እንደሆነ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የፋይናንስ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ደመረ አሰፋ የሰጡንን መረጃ እንደሚከተለው አጠናቅረነዋል።

አቶ ደመረ እንደሚገልፁት፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በከፍተኛ ኢንቨስትመንት የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት የሚገነባ እና ከፍተኛ ፋይናንስ የሚያንቀሳቅስ ተቋም ሲሆን የሀገሪቱን የብልጽግና ጉዞ እውን ለማድረግ የተለያየ ዘውግ ያላቸው ግንባታዎችን ያከናውናል፤ የግንባታ ግብዓቶች ግዢና የተለያዩ ሽያጮችን ይፈጽማል። እነዚህን ተግባራት ለማከናወን የሚያስፈልገውን ገንዘብ ከተለያዩ አካላት በማፈላለግ ለተቋሙ ሥራ አመራር ቦርድ አቅርቦ በማስፀደቅ ሥራ ላይ ያውላል።

ተቋሙ ሥራዎቹን ለማከናወን ከሚጠቀምባቸው የገንዘብ ምንጮች የመጀመሪያው የኃይል ሽያጭ መሆኑን የተናገሩት አቶ ደመረ፤ ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ሀገራት ደንበኞቹ ኃይል በማቅረብ ገቢ እንደሚያገኝ ተናግረዋል። ሁለተኛው የፋይናንስ ምንጩ ደግሞ የሀገር ውስጥ ብድር ነው። ይህም ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር በመተባበር የኩፖን ቦንድ ሽያጭ በማከናወን የሚገኝ ሲሆን በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ሰጪነትና በገንዘብ ሚኒስቴር ዋስትና ሰጪነት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ብድር እንደሚመቻች ገልፀዋል። ሶስተኛው ከውጭ ሀገራት በተለይም ከልማት አጋሮች የሚገኝ ብድር እና ስጦታ ነው። ከእነዚህ በተጨማሪ ተቋሙ ሌሎች አነስተኛ የፋይናንስ ምንጮች ቢኖሩትም በዋናነት የተቋሙ ፋይናንስ የተመሰረተው ከላይ በተጠቀሱት ምንጮች ላይ ነው።

ተቋሙ ወጪዎችን በራሱ ገቢ የመሸፈን አቅሙ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል የሚሉት ሥራ አስፈፃሚው፤ ገቢውን የሚፈለገው ደረጃ ላይ ለማድረስ ብዙ መሥራትን ይጠበቅበታል ብለዋል። አብዛኛዎቹ ተስፋ የተጣለባቸው የተጀመሩ የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች ሙሉ ለሙሉ ተጠናቀው ወደ ሥራ ሲገቡ ተቋሙ ማመንጨት የሚገባውን ኃይል አመንጭቶ ወደ ገበያ በማስገባት ገቢውን በከፍተኛ ደረጃ የሚያሳድግበት ሰፊ ዕድል ይፈጠራል።

ኢትዮጵያ ኃይል የምትሸጥብት ታሪፍ በዓለም ርካሽ ከሚባሉት ውስጥ እንደሆነ የተናገሩት አቶ ደመረ፤ በዚህ የተነሳ ዘርፉ የሚጠበቀውን ጥቅም አለማግኘቱን ያነሳሉ። ሀገሪቱ በተለይም በኢንዱስትሪው ዘርፍ ያላትን የማደግ ፍላጎት ለማፋጠን የኃይል ሽያጭ ዋጋን በመቀነስ ኢንቨስትመንትን የመሳብ አቅጣጫን እንደምትከተል ገልጸው ይህ ሁኔታ በዚህ የሚቀጥል መሆን የለበትም ይላሉ። ተቋሙ ለግንባታና ለማስፋፊያ ሥራዎች የሚበደረውን ከፍተኛ ገንዘብ መመለስ የሚችለው ያመረተውን ኃይል በተመጣጣኝ ታሪፍ መሸጥ ሲችል በመሆኑ የታሪፍ ማሻሻያ ሊደረግ ይገባል ባይ ናቸው።

ተቋሙ የገበያ አማራጮችን የማስፋትና ወጪን የመቀነስ ተግባራትን እያከናወነ እንደሚገኝም ጠቅሰዋል። በተለይም የኤሌክትሪክ ኃይልን ለጎረቤት ሀገራት ኤክስፖርት እያደረጉ የገቢ አቅምን የማሳደጉ ሁኔታ ከዓመት ወደ ዓመት እያደገ መምጣቱን በመጥቀስ ከኬንያ ጋር የተጀመረው የኃይል ሽያጭ ስምምነት አንዱ ማሳያ ነው ይላሉ። ኃይልን ኤክስፖርት ማድረጉ እንደ ተቋም አንድ የገቢ ምንጭ ሲሆን እንደሀገር ደግሞ የውጭ ምንዛሪ እጥረትን የሚቀርፍ ነው። በተመሳሳይ ለሌሎች ጎረቤት ሀገራትም ተደራሽ የማድረግ ሥራ ለመሥራት እንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል።

በሀገር ውስጥ የከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚ የሆኑና ከተቋሙ ጋር በቀጥታ የኃይል ግዢ የፈጸሙ ከ132 ኪሎ ቮልት በላይ ተጠቃሚ የሆኑ የኢንዱስትሪ ደንበኞች እንዳሉ ጠቅሰዋል። የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎትም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የሚያመርተውን ኃይል እየገዛ ለኅብረተሰቡ የማዳረስ ሥራዎችን ይሠራል። ትልቁ ገቢ የሚገኘው በኤሌክትሪክ አገልግሎት አማካኝነት ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ከሚውለው ሽያጭ ነው። አገልግሎት ሰጪው ተቋም ደንበኞቹን እያሳደገ በሄደ ቁጥር የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኤሌክትሪክ የማቅረብ አቅም እያደገ ስለሚሄድ ከተቋሙ ጋር በቅርበት እና በትብብር እየተሠራ ነው ብለዋል።

ከዚህ በተጨማሪ ተቋሙ ለኢትዮ ቴሌኮም፣ ለሳፋሪኮምና መሰል ተቋማት ኦፕቲካል ፋይበር «OPGW» በማከራየት ገቢ የሚያገኝ መሆኑን ተናግረዋል። ተቋሙ ገቢን ያስገኛሉ ባላቸው ተጨማሪ ምንጮች ላይ ሁሉ ዓይኑን እያማተረ እንደሚገኝ ገልጸዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ መታሰብ ያለበት የሚወጣውን ወጪ መቆጠብ እና ለታለመለት ዓላማ ብቻ መዋል እንዳለበት ክትትል ማድረግ እንዳለበት አጽንኦት ሰጥተው ይገልጻሉ። በዚህ ረገድ ምን እየተሠራ እንደሆነና የፋይናንስ ጤናማነቱን ለማረጋገጥ ተቋሙ ስለተገበራቸው አሠራሮች በቀጣይ ሳምንት በይደር አቆይተን እንመለስበታለን። እስከዚያው መልካም ሳምንት!

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል